የኢትዮጵያ ብሔራዊ አንድነት አርበኞች ግንባር
(ኢ.ብአአግ)

Ethiopian National United Patriotic Front
(ENUPF)

# ድርጅታዊ መግለጫ

ግንቦት ፲፬ ቀን ፲፱፻፺፰ ዓ.ም.

## ኅብረት ወይስ ውድቀት

ኅብረት ለነፃነት እና ለዴሞክራሲ የሚል አዲስ የኢሕአዴግ ተቃዋሚ ኅብረት መቋቋሙን በስብሰባ ላይ እንዲገኙ ጥሪ ተደርጎላቸው የተሳተፉና፣ ከግንቦት ፲፩ እስከ ፲፬ ፲፱፻፺፰ ዓ.ም. ባካሄዱት ስብሰባ፣ ኅብረቱንም መሥርተው፣ አመራር መርጠው በጋራ ትግል ለተሳተፍ መስማማታቸውን በድረገጾች በዛሬው እለት መውጣቱን ደርሰንበታል።

በመሠረቱ የኢትዮጵያ ብሔራዊ አንድነት አርበኞች ግንባር /ኢ.ብአአግ/ የኢትዮጵያን ነፃነትና አንድነትና በኅብረት ለማስከበር የሚደረገውን ጥረት ሁሉ ይደግፋል። ነገር ግን የዚህ ስብሰባ አጀንዳ በሚስጢር ተይዞና በስብሰባው ላይ ድርጅታችን ተገኝቶ እንዲሳተፍ ያልተጋበዘበት ምክንያት አልገባንም።

ምናልባትም የወያኔ እና የሻዕቢያ እጅ ይኖርበት ይሆናል በማለት ጠርጥረናል። ሀቀኞቹ አርበኞች በኢትዮጵያ ነፃ ምድር ላይ ደማቸውን እያፈሰሱ፣ አጥንታቸውን እየከሰከሱ፣ ኢትዮጵያን ከባንዳ የግፍ አገዛዝ ነፃ ለማውጣት በመረባረብ ላይ ስለሆኑ፣ የነሱ ተወካዮች ተጋብዘው ቢሆን ኖሮ በውውይቱ ተካፋይ ከመሆንም አልፎ፣ የኅብረት ትግል ስልቱን በማጠናከር ወያኔን አስወግዶ፣ ዴሞክራሲያዊ አስተዳደር እንዲመሠረት የሚረዳ ጠንካራና እውነተኛ ኅብረት እንዲመሠረት ለማድረግ በተቻለ ነበር። ወደፊትም የዚህ ዓይነቱ ኅብረት እንዲመሠረት ከመታገል ግንባራችን ወደ ኋላ አይልም።

ሆኖም፣ ይህ ዛሬ ተመሠረተ ተብሎ የተነገረለት ኅብረት መሥራች ነን በማለት አሥመራ ላይ ቢሮ ከፍተው፣ የኢትዮጵያ ሕዝብ አርበኞች ግንባርን እንመራለን የሚሉ የሻዕቦያ ቅጥረኞችና የቅንጅት የሰሜን አሜሪካ የድጋፍ ኮሚቴ ተወካዮች ነን የሚሉ መገኘታቸውን ሰምተን አዝነናል። በኢትዮጵያ በረሃዎች ከወያኔ ቅጥረኛ ሠራዊት ጋር ለበርካታ ዓመታት ሲፋለሙ የቆዩት የኢትዮጵያ ሕዝብ አርበኞች ግንባር /ኢ.ሕ.አ.ግ/ አባላት የአሥመራው የኢሳያስ አፈወርቂ ተላላኪዎች አይወክሉንም በማለት በተደጋጋሚ መግለጫ ካወጡ በኋላ፣ እነዚህ ቅጥረኞች የኢሳያስ አፈወርቂ ዋና ረዳትና የቀኝ እጁ የሆነው የአቶ የማነ ገብረመስቀል በመራው ስብሰባ ላይ ተወካይ ነን ብለው መቅረባቸው አርበኛውን ስላስቆጣው በዝምታ ሊያልፈው አይችልም።

ለኢትዮጵያ ሕዝብ ግልጽ እንዲሆን የምንፈልገው ጉዳይ ቢኖር፣ የኢትዮጵያ ብሔራዊ አንድነት አርበኞች ግንባር /ኢ.ብ.አ.አ.ግ/ ከኢትዮጵያ ሕዝብ አርበኞች ግንባር /ኢ.ሕ.አ.ግ/ ጋር በውኅደት መታገላቸውን ነው።

ቀደም ሲል በሳይንቲስት እንጅነር ቅጣው እጅጉ ተመስርቶ የነበረው የአርበኞች ግንባርና በኮሎኔል አሥራት ቦጋለ ይመራ የነበረው የአርበኞች ግንባር ተዋህዶ የኢትዮጵያ ብሔራዊ አንድነት አርበኞች ግንባር በሚል የመጠሪያ ስም ከታወቀ በኋላ፣ በኢትዮጵያ ውስጥ ከሚንቀሳቀሰው ከኢትዮጵያ ሕዝብ አርበኞች ግንባርና ከሌሎችም ጋር በመተባበር በተለያዩ የኢትዮጵያ ክፍለ ሀገሮች የሚንቀሳቀሰውን አርበኛ፣ ዛሬ ተመሠረተ በተባለው ኅብረት ውስጥ የተሳተፉትን የአርበኞች ተወካዮች ነን የሚሉትን አስመሳዮች አያውቃቸውም። በስሙም እንዲጠቀሙ አይፈቅድላቸውም። አቶ ኢሳያስ



P. O. Box 2206, Washington, DC 20013 • U.S.A. •
Tel. (202) 785-1618, Fax (703) 352-8612
www.enupfforethiopia.org

አፈወርቂም በበኩሉ በወያኔ ምትክ ሌላ የዘጠኝ የቋንቋ መንግሥታት በኢትዮጵያ የማቋቋም አላማውን ከፍፃሜ ለማድረስ በከንቱ ሲኳትን ይከርማል እንጂ ኢትዮጵያ አትበታተንም።

ሌላው አሳዛኝ ሁኔታ፣ የሕዝብን ድምጽ አናስደፍርም በማለታቸው ለእስር የተዳረጉት የቅንጅት መሪዎች በእስር ላይ እያሉ፣ የቅንጅት ደጋፊዎች ነን ባዮች፣ ከአሥመራ ተነስቼ እዋጋለሁ ከሚለው የአስመሳይ አርበኞች ድርጅት ጋር መሰለፋቸው የወያኔን የሀሰት ክስ እውነት በማስመሰል እንዲያጠቃቸው የተቀነባበረ ሤራ ስለሚመስል ነው። ለማንኛውም የመጨረሻውን ውሳሜ ለኢትዮጵያ ሕዝብ እንተዋለን። ለጊዜው ግን አንዳንድ የሚነሱ ጥያቄዎች አሉ። ፩. የቅንጅት ተወካይ ነኝ የሚለው ቡድን በሻዕቢያ ካድሬ በተመራው ስብሰባ ተገኝቶ እንዲደራደር ከቅንጅት መሪዎች በእውነት ውክልና ተሰጥቷልን? ፪. የኢትዮጵያ ዴሞክራሲያዊ ኃይሎች ኅብረት /ኅብረት/ ተወካዮች በአዲሱ “ኅብረት ለነፃነት እና ለዴሞክራሲ” ድርጅት ምስረታ ላይ ተገኝተው በሂደቱ ባለመስማማት መድረኩን ረግጠው ከወጡ በኋላ፣ እንደ መሥራች አባል አድርጎ መግለጫ ማውጣት ማንን ለማታለል ይሆን? ፫. ለኢትዮጵያ አንድነትና ነፃነት የሚታገሉትን ሕብረብሔር የሆኑ ድርጅቶችን፣ የሲቪክ ማሕበራትን፣ የሰብአዊ መብት ተከራካሪዎችን ለምን አልጋበዙም? በመጨረሻም፣ ይህን ዓይነት አሠራር ከመለስ ዜናዊ የባንዳ ቡድን እንቅስቃሴ ጋር የተለየ የሚያደርገው ምን ይሆን? ማንንስ ለማዘናጋት ይሆን? ብለን እንጠይቃለን።

የኢትዮጵያ ሕዝብ ሆይ

በፈጣሪ አምላካችን እገዛ ወገናችንን እና እናት ሀገራችን ከወያኔ ጎሰኛ አገዛዝ ነፃ እንድትወጣና ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት እንዲመሠረት በሚደረገው ትግል እራስህን በአርበኛ ልጆችህ ብርታትና መስዋዕትነት እንደምትወጣው አንጠራጠርም። ኢ.ብ.አ.አ.ግ እራሱን የኢትዮጵያ ሕዝብ አርበኞች ግንባር መሪ ነኝ በማለት ከአስመራ ከሚቀላውጠው ቡድን ጋር ምንም ዓይነት ግንኙነት እንደሌለውና በሀረሃ ከሚታገለው የኢ.ሕ.አ.ግ አርበኛ ጋር ግን በተጨባጭ ተግባር በአንድነት የሚሠራ መሆኑን እናረጋግጥልሃለን። ወደፊትም ሀገር ወዳድ ድርጅቶች በአንድነት ጎራ ተሰባስበው ክብርህንና መብትህን ጠብቀው እራስህ የምትሻውን መንግሥት እንድትመሠርት አርበኛው ዘብ ቆሞ እንደሚጠብቅ ቃል ይገባልሃል።

ድል ለኢትዮጵያ ሕዝብ!
ኢትዮጵያ በእግዚአብሔር ቸርነት ለዘለዓለም ትኖራለች!
የኢትዮጵያ ብሔራዊ አንድነት አርበኞች ግንባር
ማዕከላዊ ኮሚቴ



P. O. Box 2206, Washington, DC 20013 • U.S.A. •
Tel. (202) 785-1618, Fax (703) 352-8612
www.enupfforethiopia.org